1·0/344/12
14 ነሐሴ 2004

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Revenues and Customs Authority

ለአ/አ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአ/አ የንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
ለሚሌ ቅ/ጽ/ቤት
ለባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት
ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት
ለጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት
ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት
ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት
ለሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት
ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመመሪያ ማሻሻያ ስለመላክ</u>

የጉሙሩክ ዲክለራሲዮን አቀራረብን ለመወሰን የወጣውን መመቀሪያ ቁጥር 33/2001ን ማሻሻል በማስፈለጉ ተሻሽሏል፡፡

ስለሆነም ማሻሻያ መመሪያው ቁጥር 72/2004 ከዚህ ጋር የተላከ ስለሆነ የተሻሻለውን ጉዳይ በተመለከተ በማሻሻያ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

25/11/04

ከሠላምታ ጋር

መላኩ ፈንታ
ዋና ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>፣

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ
- ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ሥራዎች ዘርፍ
  <u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>
- ለኢትዮጵያ አየር መንገድ
  <u>አዲስ አበባ</u>

## የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አቀራረብን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 33/2001ን ለማሻሻል

## የወጣ መመሪያ ቁጥር 72/2004

የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አቀራረብን ለማሻሻል የወጣውን መመሪያ ቁጥር 33/2001 ማሻሻል በማስፈለጉ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አቀራረብን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 33/2001ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 72/2004 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

   የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አቀራረብን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 33/2001 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   1) በትርጉም ክፍሉ ከአንቀጽ 2(23) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (24) ተጨምሯል

      (24) "የበረራ ሠራተኛ" ማለት በአለም አቀፍ የአየር መንገድ በረራ በጉዞ ላይ ባለ አይሮፕላን ውስጥ የሚሰራ አብራሪ፣ የበረራ አስተናጋጅ፣ የበረራ ቴክኒሻን ወይም የበረራ ደህንነት ሠራተኛ ነው፡፡

   2) አንቀፅ 14 ሁለት ንዑስ አንቀፆች እንዲይዝ ተደርጐ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

14. <u>አረንጓዴ ማስፊያ</u>

   1. ማንኛውም መንገደኛ ዕቃ ካልያዘ ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች መያዙን በቃል በማረጋገጥ ወይም/ እና በአካል በአረንጓዴ ማስፊያ በኩል ማስፍ ይችላል፡፡

      ሀ. አንድ CD ማጫወቻ ያለው ቴፕሪከርደር ወይም አንድ ሬዲዮ፣

      ለ. አንድ ዲጅታል ፎቶ ካሜራ ወይም/እና ቪዲዮ ካሜራ፣

      ሐ. አንድ የሞባይል ቀፎ፣

      መ. ከሁለት ሊትር ያልበለጠ ለግሉ የሚጠቀምበት ማንኛውም የአልኮል መጠጥ፣

      ሠ. በቁጥር ከ20 ፓኬት ያልበለጡ ሲጋራዎች ወይም/እና 250 ግራም ትምባሆ፣

      ረ. የንግድ መጠን የሌላቸውና ዓይነታቸው የተለያየ መጽሔቶች፣መጽሐፍቶች/ ምስልና ድምፅ የተቀረፀባቸውና ያልተከለከሉ ካሴቶችና ሲዲዎች፣

      ሰ. ተመመሳሳሽ መንገደኛ ካልሆነ ከ100 ግራም ያልበለጡ፤ ተመላላሽ መንገደኛ ለሆነ ከ50 ግራም ያልበለጡ የግል ጌጣጌጦች፣

      ሸ. መጠኑ ከ0.5 (ግማሽ) ሊትር ያልበለጠ ሽቶ፣

      ቀ. በሐኪም ትዕዛዝ ለግል ጥቅም የሚውሉ መድሐኒቶች፣

መላኩ ፈንታ
ዋና ዳይሬክተር

በ. የንግድ መጠን የሌላቸው አልባሳት

ተ. እንደ CDMA፣

ቸ. የውጭ አገር ነዋሪ ከሆነ እንደ ላፕቶፕ፣

2. የበረራ ሠራተኞች ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም እንደማንኛውም መንገደኛ የሚቆጠሩና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተዘረዘሩትን ዕቃዎች በአረንጓዴ ማለፊያ ይዘው ማለፍ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1/መ/ የተጠቀሰው የአልኮል መጠጥን በተመለከተ ከአንድ ሊትር በላይ አይፈቀድላቸውም፡፡

3) የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ አንቀፅ 23 ሆኖ ተጨምሯል፡፡

23. <u>ባለማወቅ በስህተት ስለሚፈፀሙ ጉዳዮች</u>

1. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ከፍተኛ ባለሀብቶች፣ ኤክስፓርተሮች፣ የውጭ መንግሥታት ከፍተኛ ልዑካን እና የመሳሰሉት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ሁኔታዎች በስህተትና ባለማወቅ ተላልፈው በሚገኙበት ጊዜ በመንገደኛ ይዘዋቸው የሚገቡ ወይም የሚወጡ ዕቃዎችን በተመለከተ የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

2. የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ውሳኔ እስከሚሰጥ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቀረጥና ታክስ መጠን በዋስትና /ዲፖዚት/ በማስያዝ እቃውን ሊለቅ ይችላል፡፡ ዋስትና /ዲፖዚት/ ማስያዝ በማይቻልበት ጊዜ የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ዕቃው በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ስር ይቆያል፡፡

3. የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሰጡትን ውሳኔ በየጊዜው ለዋናው መ/ቤት ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡

4) የመመሪያው አንቀፅ 23፣24 እና 25 እንደቅደም ተከተላቸው አንቀፅ 24፣25 እና 26 ሆነዋል፡፡

27. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ የሆናል፡

አዲስ አበባ-------------------ቀን 2004 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር